በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የጅማ ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

ዩኒቨርሲቲው የተመደበለትን የመደበኛ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል::

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የዩኒቨርሲቲው ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል።

ኦዲታችን፡-

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታኝ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል::

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ዩኒቨርሲቲው ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- ☐ጪ/የዕርዳታ/ የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. በዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢና የተለያዩ ኮሌጆች ከመማር ማስተማሩ ሂደት የውስጥ ገቢን ለማመንጨት የሚከፈሉ ክፍያዎች (ለፕሮጀክት ሥራ ክፍያ፣ ለተከታታይ፣ ርቀትና ክረምት ትምህርት ክፍያ፣ ለሥራ ጫና ክፍያ፣ ለፈተና ክፍያ፣ ለመመረቂያ ጽሁፍ መገምገሚ ክፍያ ...) በመመሪያው መሰረት በቦርድ መወሰን ሲገባው ዩኒቨርሲቲው ባዘጋጀው የክፍያ ተመን መሰረት በድምሩ ብር 4,337,514.02 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣
2. በጤና ኢንስቲትዩት ለስፔሻሊስት ሀኪሞች የስራ ጫና ክፍያ በሚል በማኔጅመንት ውሳኔ በበጀት ዓመቱ ብር 4,370,602.00 ከመመሪያ ውጭ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣
3. በዩኒቨርሲቲው ላይዘን ቢሮ በቅድሚያ የተከፈለው ውሎ አበል ብር 22,226.00 በተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ ሰራተኞች ከመስክ በሚመለሱበት ጊዜ የውሎ አበል ማወራረጃ ቅጽ ተሞልቶና በሚመለከተው ኃላፊ ፀድቆ በወጪ መመዝገብ ሲገባዉ አላግባብ በቀጥታ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፣

4. የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ከኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የተላኩ የጤና ኤክስቴሽን ባለሙያዎችን ለ16 ቀን ለማሰልጠን ከክልሉ ጤና ቢሮ ጋር ውል የገባ ሲሆን ከክልሉ ከተገኘው ገቢ ላይ በድምሩ ብር 276,999.00 ከዋናዉ ግቢና ከቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የተውጣጡ የዩኒቨርሲቲው ሠራተኞች ወደ ሶኮሩና ሊሙ ወረዳዎች የሄዱበት በሚል በቀጥታ ወጪ ለእያንዳንዳቸዉ የ32 ቀን ውሎ አበል የተከፈላቸው ሲሆን በውሉ መሰረት ስልጠናዉ የሚካሄደው ጅማ ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ሆኖ ሣለ ወደ ወረዳዎች መጓዝ ያስፈለገበትን ሁኔታ የሚገልጽ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ የክፍያውን አግባብነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፤

5. በተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ ለህንድ መምህራን የተከፈለ የትራንስፖርት ክፍያ ብር 13,813.57 በቅጂ (ኮፒ) የአውሮፕላን ቲኬት የተወራረደ መሆኑ፤

6. ግዥዉ በዕቅድ ተይዞ በግልፅ ጨረታ በጥቅል መገዛት ሲገባው በዋናው ግቢ ብር 2,902,161.39፤ በሶሻል ሳይንስ ኮሌጅ ብር 542,362.15 እና በጤና ኢንስቲትዩት ብር 1,312,070.76 በድምሩ በብር 4,756,594.30 የተለያዩ ዕቃዎች ግዢ በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ የተፈጸመ መሆኑ፤

7. በድምሩ ብር 22,898,293.64 የግንባታ መያዣ ሂሰብ (Retention) ከህንጻ ስራ ተቋራጮች የተቀነሰ ቢሆንም በመመሪያው መሰረት በሂሳብ መደብ 5061 በተከፋይ ሂሳብ ተመዝግቦ ሪፖርት መደረግ ሲገባዉ ምንም አይነት የሂሣብ ምዝገባ ያልተከናወነና የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ውስጥ ተካቶ ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ፤

8. በጊዜ ገደቡ ያልተወራረደ ብር 1,411,723.83 ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚገኝ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ከላይ በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሣ በእኛ አስተያየት የዩኒቨርሲቲው የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

<u>ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች፤</u>

ምንም እንኳን በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ባይኖራቸውም መሠረታዊና ጉልህ የሆኑ የውስጥ ቁጥጥርና የአፈጻጸም ድክመቶች ቀጥለው ተመልክተዋል፡፡

1. በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ከተለያዩ ዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች የቅድመ-ግብር ክፍያ (Withholding Tax) ብር 17,905.82 ያልተሰበሰበ መሆኑ፤

2. በጤና ኢንስቲትዩት እና በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ከተለያዩ ዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ብር 24,079.02 ያልተሰበሰበ መሆኑ፤
3. ለዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት የተፈቀደለት በጀትና በሥራ ላይ የዋለው ሂሣብ ሲነጻጸር በተለያዩ ሂሣብ መደቦች ከመደበኛ በጀት ብር 10,367,290.33 እና ከውስጥ ገቢ 742,742.28 በድምሩ ብር 11,110,032.61 ሥራ ላይ ያልዋለ (ያልተሰራበት) መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

<u>ሌሎች ጉዳዮች፤</u>

1. የዩኒቨርሲቲው የንብረት አጠባበቅና አመዘጋገብ ኦዲት ሲደረግ፤

<u>በዋናው ግቢ፣</u>

- መወገድ ሚገባቸው 3 የዉሃ ማፍያ ማሽኖች፣ የተለያዩ ቁርጥራጭ ብረቶች፣ 116 ኢፕሰን ፕሪንተሮች፣ 216 ዲቫይደሮች፣ 118 ታጣፊ ወንበር እና 11መኪናዎች ያልተወገዱ መሆኑ፤
- በተማሪዎች ምግብ ቤት ከ10 አመት በላይ አገልግሎት ሳይሰጡ የተቀመጡ 4 (አራት) ፍሪጆች የሚገኙ መሆኑ፤

<u>በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፤</u>

- የተለያዩ UPS በቁጥር 433፣ የኮምፒዩተር ጠረጴዛዎች በቁጥር 78 እና ወንበሮች በቁጥር 50 ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- የዉሃ ማጠራቀሚያ ፕላስቲኮች በቁጥር 323 ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤፤
- የተለያዩ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፣ ኮምፒዩተሮች፣ የእንግዳ ወንበሮች እና UPS ሳይወገዱ በአሮጌ ዕቃዎች ግምጃ ቤት (ሳልቫጅ ስቶር) የሚገኙ መሆኑ፣

<u>በስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፤</u>

- ቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች በአንድ ላይ ተቀላቅለዉ በአንድ መጋዘን ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣
- ከሶስት አመት በላይ ያለአገልግሎት የተቀመጡ በርከት ያሉ የሴቶች ጫማና አልባሳት በዕቃ ግምጃ ቤት የሚገኙ መሆኑ፣

<u>በግብርናና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ፤</u>

- ቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች በአንድ ላይ ተቀላቅለዉ በአንድ መጋዘን ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣
- በብልሽት አገልግሎት የማይሰጥ አንድ የማባዣ ማሽን በዕቃ ግምጃ ቤት የሚገኝ መሆኑ፣
- በተማሪዎች ምግብ ቤት አገልግሎት የማይሰጡ የተበላሹ አራት ስቶቮች የሚገኙ መሆኑ፤

2. የ7 (ሰባት) ተሽከርካሪዎች የኪ/ሜ ቆጣሪ (ጌጅ) የማይሰራ መሆኑና ተሽከርካሪዎቹ በሄዱበት ኪ/ሜ ተገምቶ ነዳጅ የሚሞላ መሆኑ፤
3. በዩኒቨርሲቲው የሰው ኃይል መዋቅር መሠረት 12 የኦዲት ባለሙያዎች የሚያስፈልግ ሲሆን በአሁኑ ወቅት 3 የኦዲት ባለሙያዎች ሲኖሩ ከዩኒቨርሲቲው የውስጥ ኦዲት የሰው ኃይል መዋቅር ጋር ሲነፃፀር 9 የኦዲት ባለሙያዎች በቅጥር ያልተሟሉ መሆኑ፤

በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የጅማ ዩኒቨርሲቲ

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

መግቢያ፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የጅማ ዩኒቨርሲቲ የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዩኒቨርሲቲውን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፤

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሰረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን ፣

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ ሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን፣ ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

ይሁን እንጂ ኦዲቱ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡ የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የተቋሙ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

የጅማ ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. የወጪ ሂሳብ፤

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች ተቋሙ ለተጠቀመበት አገልግሎት መዋሉን፤ የዕቃና አገልግሎት ግዥ በመንግስት የግዥ መመሪያ መሠረት መፈጸሙን፣ የተገዙት ዕቃዎች ገቢ መደረጋቸውንና እንዲሁም ለታቀደለት ዓላማ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

1.1 ደመወዝና ተዛማጅ ክፍያዎች፣

1.1.1.1 ግኝት፤ በቦርድ ሳይፀድቅ ከውስጥ ገቢ የተከፈለ የጥቅማጥቅም ክፍያ፤

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006 አንቀፅ 3 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢን ጥቅም ላይ ማዋል የሚችሉት ፀንተዉ የሚሰራባቸዉን ሕጎችና መመሪያዎች መሰረት በማድረግ መሆን እንዳለበት ይገልፃል፡፡ እንዲሁም የዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ተራ ቁጥር 2 ፊደል ሀ የውስጥ ገቢ መጠን እንዲሁም ገቢዉን ለማመንጨት የሚወጣው ወጪ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ቦርድ እንደሚወሰን ይገልጻል፡፡ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/75/390 በቀን 13/08/03 የደመወዝ ስኬል አወሳሰንን በተመለከተ የማንኛዉም የመንግስት መስርያ ቤት ሠራተኞች የደመወዝ ስኬልና ጥቅማጥቅም ቀርቦ የሚወሰነዉ በሚኒስትሮች ምክር ቤት መሆን እንዳለበትና በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም በራሱ/በቦርድ የሰራተኞች የደመወዝ ስኬልና ጥቅማጥቅሞችን መፍቀድ ወይም መለወጥ እንደማይቻል ገልጿል፡፡ በዚሁ መሠረት ኦዲት ሲደረግ፤

- **በዋና ግቢ** ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ ተቋማት እና ዩኒቨርሲቲዎች ጋር የሶፍትዌር ደቨሎፐመንት ስራ ለመስራት ውል በመግባት ከሚያገኘው ገቢ 20% ለዩኒቨርሲቲው የውስጥ ገቢ ሂሳብ ገቢ እንዲደረግና 80% ደግሞ ዩኒቨርሲቲው ባዘጋጀው የክፍያ ተመን (Break Down) መሰረት ለዩኒቨርሲቲው አመራሮች፣ ለፋይናንስ ሰራተኞች እና ለአይሲቲ ባለሙያዎች እንዲከፈል የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር በወሰነው መሰረት በድምሩ ብር 900,850.00 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
- **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት** የተለያዩ ላቦራቶሪ አገልግሎት ለተማሪዎች በመስጠት ከወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ብር 86,515.51፣ ከመቱ ዩኒቨርሲቲ ብር 320,423.00፣ ከወለጋ

ዩኒቨርሲቲ ብር 88,416.00 እና ከሆራይዞን ሊሙ ፕላንቴሽን ብር 44,452.80 በድምሩ ብር 539,807.31 ገቢ ያገኘ ሲሆን ከተገኘው ገቢ ላይ 6% ለአስተዳደር ሰራተኞችና 59% ለመምህራን እንዲከፈል ዩኒቨርሲቲው በወሰነው ተመን መሰረት በቀን 01/02/09 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 469463 ብር 23,692.62፣ በቀን 29/03/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 469531 ብር 38,989.15፣ በቀን 04/13/08 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 620448 ብር 30,979.82 እና በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 620430 ብር 153,739.43 በድምሩ ብር 247,401.02 በዩኒቨርሲቲው ቦርድ ሳይፀድቅ ለሠራተኞች ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣

- **በግብርናና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ** ከተከታታይና ርቀት ትምህርት ክፍል ለተለያዩ የኮሌጁ ሰራተኞች የቶፕ አፕ ክፍያ ብር 239,561.00 በኮሚቴ ውሳኔ የተከፈለ መሆኑ እና እንዲሁም ለተለያዩ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የላብራቶሪ አገልግሎት በመስጠትና በማሰልጠን ካገኘው ገቢ ውስጥ ለአስተዳደር ሰራተኞች አሎዋንስ ብር 165,236.00 በድምሩ ብር 404,797.00 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
- **በተከታታይና ርቀት ትምህርት ክፍል** በቀን 15/03/2009 በባንክ ወጭ ማስመስከሪያ ቁጥር 0848547 ብር 684,305.00 በክረምት መርሀ-ግብር ላስተባበሩ የዩኒቨርሲቲው ኃላፊዎች የስራ ጫና (over load) በማለት በዓመት አንድ ጊዜ ለሬጅስተራር ዳይሬክተር፣ ለኮሌጅ ሬጅስተራር እና ለተከታታይና ርቀት ትምህርት ሬጅስተራር 6 ክሬዲት ሃወር፣ ለዲፓርትመንት ሃላፊ(ሄድ)ና ለተከታታይና ርቀት ትምህርት ም/ዳይሬክተር 5 ክሬዲት ሃወር፣ ለፕሬዚደንት፣ ለምክትል ፕሬዚደንት፣ ለዲንና ም/ዲን፣ ለዳይሬክተር እና ለተማሪዎች ዳይሬክተር 4 ክሬዲት ሃወር፣ ለኮሌጅ የድህረ ምረቃ ሪሰርች አስተባባሪ 2 ክሬዲት ሃወር በዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ውሳኔ መሰረት ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
- **በተከታታይና ርቀት ትምህርት ክፍል** የመመረቂያ ጽሁፍ ለመፈተን ለውስጥ ፈታኝ ብር 1500፤ ለአድቫይዘር ብር 2000፤ ለሞደሬተር ብር 500፤ ፈተና ላወጡበት ለሚድ ፈተና ብር 70፤ ለፋይናል ፈተና ብር 105 ዩኒቨርሲቲው ባዘጋጀው ተመን መሰረት በድምሩ ብር 1,644,661.00 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
- **በትምህርትና ስነ ባህሪ ኮሌጅ** ለተከናወኑ ስራዎች ቲሲስ ለገመገሙበት ለውጭ ፈታኞች በተማሪ ብር 2,000፣ ለውስጥ ፈታኞች በተማሪ ብር 1,500 እና የፈተናውን ሂደት ለመሩ በተማሪ ብር 500 ዩኒቨርሲቲው ባዘጋጀው ተመን መሰረት በድምሩ ብር 284,000.00 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤

- **በህግና አስተዳደር ኮሌጅ** የተከታታይና ርቀት ትምህርት ክፍል የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪዎችን መመረቂያ ጽሁፍ ለመፈተን በተማሪ ብር 2000 በድምሩ ብር 74,000.00 ዩኒቨርሲቲው ባዘጋጀው ተመን መሰረት ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤
- **በሶሻል ሳይንስና ሒዉማንቲስ ኮሌጅ** የክረምትና የመደበኛ የድህረ ምረቃ ተማሪዎችን ቲስስ ለገመገሙበት ለውጭ ፈታኞች በአንድ ተማሪ ብር 2,000.00፣ ለውስጥ ፈታኞች በተማሪ ብር 1,500 እና የፈተናውን ሂደት ለተከታተሉት ቼርፐርሰን በተማሪ ብር 500 ተመን መሰረት በቀን 26/10/2009 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 473492 ብር 30,000.00፣ በቀን 28/10/2009 በባንክ ወጭ ማስመስከሪያ ቁጥር 473501 ብር 42,000.00፣ በቀን 22/10/2009 በባንክ ወጭ ማስመስከሪያ ቁጥር 473475 ብር 12,00.000 እና በቀን 16/10/2009 በባንክ ወጭ ማስመስከሪያ ቁጥር 473454 ብር 13,500.00 ዩኒቨርሲቲው ባዘጋጀው ተመን መሰረት በድምሩ ብር 97,500.00 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

በአጠቃላይ ከመማር ማስተማሩ ሂደት የውስጥ ገቢን ለማመንጨት የሚከፈሉ ክፍያዎች በመመሪያው መሰረት በቦርድ መወሰን ሲገባው ዩኒቨርሲቲው ባዘጋጀው ተመን መሰረት በዩኒቨርሲቲው ቦርድ ሳይፀድቅ በድምሩ ብር 4,337,514.02 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ታወቋል፡፡

1.1.1.2 ስጋት፤

ዩኒቨርስቲዉ መንግሥት ያወጣቸዉን ደንብና መመሪያዎች ተከትሎ የማይሰራ ከሆነ የመንግሥትን ገንዘብ አላግባብ ለብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡

1.1.1.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፤**

ዩኒቨርሲቲው ቀጣይነት ካላቸው የመማር ማስተማር ሂደት የሚገኙ ገቢዎችን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 39/2006 በተቀመጠው አግባብ መሰረት በየደረጃው የሚወስኑ አካላቶችን በማስወሰን ክፍያ መፈጸም ይኖርበታል፡፡

1.1.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

- የተከታታይና ርቀት ትምህርት ሥራዎች ከመደበኛ ሥራዎች በተጨማሪ ጫናን ከማስተካከላቸውም በላይ የኃላፊዎችን የቅርብ ክትትልና ልዩ እገዛ የሚሹ ስራዎች ናቸው፡፡ ስለሆነም የተከታታና ርቀት ትምህርት ስራዎች የኃላፊዎች የእለት ተእለት ሥራዎች አካል አድርጉ መውሰድ አስቸጋሪ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የተከታታይ እና ርቀት ስራዎችን ለመከታተል ለማስተባበር ስራ በመንግስት የወጣ ተመን የለም፡፡ ስለሆነም ተመን ያልወጣላቸው የመማር ማስተማር ሥራዎች የክትትልና የማስተባበር ስራዎችን ጨምሮ ተመን እንዲወጣላቸውና

አግባብነት ባለው አካል እንዲፀድቁና ሥራ ላይ እንዲውሉ ጥያቄ አቅርበናል፡፡ እየተሠራም ይገኛል፤ ቢሆንም መመሪያው ጸድቆ ሥራ ላይ እስኪውል ድረስ የስልጠና ስራው መቆም ስለማይችል ቀደም ሲል በዩኒቨርስቲው ከፍተኛ ሥራ አመራር ጉባኤ በፀደቀው የውስጥ መመሪያ መሠረት የተፈፀመ ክፍያ መሆኑን እያሳወቅን መመሪያውን ቀደም ሲል ከላክነው መጠይቅ መልስ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

- በግኝት ማስታወሻ ውስጥ የተካተቱ ሥራዎች ማለትም ፈተና ማውጣት፣ ፈተናና አሳይመንት ማረም፣ መመረቂያ ፅሁፍ መፈተን፣ መመረቂያ ፅሁፍ ማማከር፣ መመረቂያ ፅሁፍ የውጪ ፈታኝ መመረቂያ ፅሁፍ የውስጥ ፈታኝ የመሳሰሉት በመንግስት የተላከ ተመን ባለመኖሩ ወይንም ባለመካተቱ ክፍተት ይታያል፡፡ ስለሆነም ተመን ያልወጣላቸው የመማር ማስተማር ሥራዎች ተመን እንዲወጣላቸውና አግባብነት ያለው አካል እንዲፀድቁና ሥራ ላይ እንዲውሉ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ይሁን እንጂ መመሪያው ጸድቆ ሥራ ላይ እስኪውል ድረስ የስልጠና ስራው መቆም ስለማይችል ቀደም ሲል በዩኒቨርስቲው ከፍተኛ ሥራ አመራር ጉባኤ በፀደቀው የውስጥ መመሪያ መሠረት የተፈፀመ ክፍያ መሆኑን እያሳወቅን መመሪያውን ቀደም ሲል ከላክነው መጠይቅ መልስ ጋር አያይዘን ለኦዲት ባለሙያዎቹ መስጠታችንን እንገልፃለን፡፡ የመምህሩ መደበኛ ሥራ በዩኒቨርስቲው መደበኛ የትምህርት ኘሮግራሞችና መደበኛ የስራ ሰዓት የተወሰነ ተግባር ነው፡፡ ከመደበኛ ኘሮግራሞች ውጭ ለሚሰሩ ስራዎች ለምሳሌ በተከታታይና ርቀት ትምህርት ኘሮግራሞች ማለትም የርቀት የክረምትና የማታ ኘሮግራሞች መምህራን ለሚያበረክቱት ማንኛውም ሙያዊ አስተዋጽኦ ከመደበኛ የስራ ሰዓት ውጭ በዕረፍት ሰዓታቸው ለምሳሌ ማታ ከ12፡00 ሰዓት በኋላ፤ ቅዳሜ እና እሁድ እንዲሁም ክረምት በሐምሌና ነሐሴ ወራት የሚሰሩት ስራ ስለሆነ ክፍያ ይፈፀማል፡፡
- በመደበኛ ፐሮግራምም አንዳንድ ሃገር አቀፍ የክፍያ ተመን ያልወጣላቸው የካሪኩለም አካል የሆኑ ስራዎች በመኖራቸው ለምሳሌ የድህረ ምረቃ ተማሪዎችን ቲስስ ለመገምገም ለውጭ ፈታኞች፤ ለአማካሪዎች፤ ለውስጥ ፈታኞች፤ ለቼርፐርሰን ለመሳሰሉት እስካሁን ባለው አሰራር ለርቀትና የተከታታይ ትምህርት ፐሮግራም የዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት ያፀደቀው የክፍያ ስርዓት በኮሌጆችም እንዲተገበር የተደረገ እንጂ ኮሌጆቹ ያወጡት አይደለም፡፡ ይህም የካሪኩለሙ አካል የሆኑ ተግባራት ተመን ስላልወጣላቸው ሊቀሩ ስለማይችሉ በመሆኑ ነው፡፡ ሆኖም የትምህርት ሚኒስቴር ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ሃገር አቀፍ የክፍያ ተመን መመሪያ እንዲያወጣ በተደጋጋሚ በጽሁፍ መጠየቃችንን ለፌዴራል ኦዲት መስሪያ ቤቱ ማስረጃዎቹን አቅርበናል፡፡

- ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ ተቋማት እና ዩኒቨርሲቲዎችጋር የሶፍትዌር ደቨሎፐመንት ስራ ለመስራት ውል በመግባት ከሚያገኘው ገቢ 20% ለዩኒቨርሲቲው የውስጥ ገቢ ሂሳብ ገቢ እንዲደረግና 80% ደግሞ ዩኒቨርሲቲው ባዘጋጀው የክፍያ ተመን (Break Down) መሰረት ለዩኒቨርሲቲው አመራሮች፣ ለፋይናንስ ሰራተኞች እና ለአይሲቲ ባለሙያዎች እንዲከፈል የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር በወሰነው መሰረት በድምሩ ብር 900,850.00 ክፍያ ተፈፀመ ለተባለው በቅድሚያ ዩኒቨርሲቲው ይህን የትብብር ፕሮጀክት ለመስራት ዓላማ ያደረገው፡-
  - ✓ የትምህርት ሚኒስቴር ነባርና አቅም ያላቸው ዩኒቨርሲቲዎች ታዳጊ ዩኒቨርሲቲዎችን እንዲደግፉና አብሮ የመስራት ባህል እንዲዳብር የሰጠውን አቅጣጫ፤
  - ✓ የዩኒቨርሲቲውን በጎ ገፅታ ግንባታ ለማጎልበት፤
  - ✓ በዘርፉ ያሉን ባለሙያዎች በገበያው ውስጥ ካላቸው ተፈላጊነት በመነሳት ዩኒቨርሲቲውን ለቀው እንዳይሄዱ ማቆየት እንዲቻል ታሳቢ ያደረገ ሆኖ በተጨማሪም
  - ✓ የዩኒቨርሲቲውን የውስጥ ገቢ በማሳደግ የመደበኛ በጀት ክፍተትን ለመሙላት በሚደረገው ጥረት አስተዋፅዖ ስለሚያደርግም ጭምር ነው፡፡

በ□ህም በርካታ ዩኒቨርሲቲዎችን ከፍተኛ ወጪ ከማውጣት ከማዳኑም በላይ የዕውቀት ሽግግር በማድረግ ዩኒቨርሲቲዎቹ የቴክኖሎጂው ከፍተኛ ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ስራዎቹም እ□ተሰሩ ያሉትና የክፍያ አፈፃፀሙም በዩኒቨርሲቲውና ፕሮጀክቱ በሚሰራላቸው ተቋማት ስምምነትና በተዘጋጀው የፕሮጀክት ዝርዝር ሰነድ መሠረት ነው፡፡ የክፍያ አፈፃፀሙም በሁለት መልኩ ነው፡፡ አንደኛ□ ቦታው ድረስ ሄደው ለሚያከናውኑት ስራ በውሉ ውስጥ በተቀመጠው ተመን መሠረት በውሎ አበል ሲሆን ሁለተኛው የክፍያ ተመን በፕሮፌሽናል ክፍያ ተመን መሠረት ነው፡፡ በዚህም በግኝቱ ላይ ከተጠቀሱት ውስጥ 748,850.00 (ሰባት መቶ አርባ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ሃምሳ ብር) በፕሮፌሽናል ክፍያ መሠረት የተከፈለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 248,614.55 (ሁለት መቶ አርባ ስምንት ሺህ ስድስት መቶ አስራ አራት ብር ከሃምሳ አምስት ሳንቲም) በፅብር መልክ ለመንግስት ገቢ የተደረገ መሆኑን፤ ብር 152,000.00 (አንድ መቶ ሃምሳ ሁለት ሺህ ብር) በውሎ አበል የተከፈለ ሲሆን የቀን አበል ተመኑም በፕሮጀክቱ ስምምነት መሠረት የተፈፀመ እንዲሁም ለዩኒቨርሲቲው በውስጥ ገቢ መልክ የውሉ ዋጋ 20 በመቶ ገቢ መደረጉንና በአሁኑ ወቅት ደግሞ ጁኸው መጠን 24 በመቶ መድረሱን□እየገለፅን ከተቋማቱ ጋር በወቅቱ የተገቡትን □□ል ስምምነቶች 114 ገፅ ለኦዲት ባለሙያዎቹ ማቅረባችንን□እንገልፃለን፡፡

- የተለያዩ የዩኒቨርሲቲው ኮሌጆች ለተለያዩ ተቋማት የላቦራቶሪ ስልጠናና የፍተሻ አገልግሎት ሲሰጡ በሃገር ዓቀፍ ደረጃ በወጣው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የውስጥ ገቢ አጠቃቀም መመሪያ ላይ ዝርዝር የአከፋፈል ስርዓት ባለመዘርጋቱ የማሰልጠኛ ክፍሎቹ ስልጠናውን

(አገልግሎቱን) ከጠየቁ ተቋማት ጋር በገቡት ውል መሰረት ወይም የውስጥ መመሪያ በማዘጋጀት ክፍያውን የሚፈፅሙ ሲሆን በዚህ ዙሪያ ወጥ መመሪያ እንዲወጣ የትምህርት ሚኒስቴር በደብዳቤ ተጠይቋል፡፡

1.1.1.5 የኦዲተሩ አስተያየት፤

የክፍያ ተመን ላልወጣላቸው ክፍያዎች ለዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ቦርድ በማቅረብና በማፀደቅ ክፍያ መፈጸም ይገባል፡፡

1.1.2.1 ግኝት፤ ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ የስራ ጫና ክፍያ፤

በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 3 እንደተደነገገው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን ልዩ የሥራ ባሕሪ መሠረት በማድረግ ልዩ ልዩ የደመወዝ ስኬሎች እንዲጠኑ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሲፈቀድ ኤጀንሲው አጥንቶ ለምክር ቤቱ ለውሳኔ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም አፈፃፀሙን ይቆጣጠራል ይላል፡፡ በተጨማሪም የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/71/390 በቀን10/18/8/03 በጻፈው ደብዳቤ የመንግስት መስሪያ ቤት ሠራተኞች ደመወዝ ስኬል እና ጥቅማጥቅም ቀርቦ የሚወሰነው በሚኒስትሮች ምክር ቤት በመሆኑ በቦርድ ወይም በማኔጅመንት የሚወሰንና የሚከፈል ክፍያ ተቀባይነት እንደሌለው ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- **የጤና ኢንስቲትዩት** ለስፔሻሊስት ሀኪሞች የስራ ጫና ክፍያ በሚል በማኔጅመንት ውሳኔ በበጀት ዓመቱ ብር 4,370,602.00 ከመመሪያ ውጭ ክፍሎ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ በሠንጠረዡ ተመልክቷል፡፡

ተ.ቁ	ቀን	የቫውቸር ቁጥር	የክፍያው ምክንያት	የገንዘብ መጠን
1	19/01/09	134659	የሀምሌና ነሃሴ ወር የስፔሻሊስት ሃኪሞች የስራ ጫና የተከፈለ	716,880.00
2	21/04/09	134682	የመስከረምና ጥቅምት ወር የስፔሻሊስት ሃኪሞች የስራ ጫና	744,442.00
3	11/07/09	588897	የህዳርና ታህሳስ ወር የስፔሻሊስት ሃኪሞች የስራ ጫና	765,600.00
4	21/09/09	589269	የጥርና የካቲት ወር የስፔሻሊስት ሃኪሞች የስራ ጫና የተከፈለ	709,920.00
5	12/10/09	589414	የመጋቢትና ሚያዝያ ወር የስፔሻሊስት ሃኪሞች የስራ ጫና	702,960.00
6	19/10/09	589551	የግንቦትና ሰኔ ወር የስፔሻሊስት ሃኪሞች የስራ ጫና የተከፈለ	730,800.00
			ድምር	4,370,602.00

1.1.2.2 ስጋት፤

ከደንብና መመሪያ ውጪ ክፍያ መፈጸም የመንግሥት ገንዘብ አግባብ እንዲባክን ያደርጋል፡፡

1.1.2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

ለሥራ ጫና በሚል የተፈጸመው ክፍያ ከመመሪያ ውጪ በመሆኑ ክፍያው እንዲቋረጥ የሥራ አመራሩ ተገቢ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

1.1.2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

ለእስፔሻሊስት ሀኪሞች የሥራ ጫና በየወሩ 58 ሰዓት እንደከፈል የተወሰነበት ምክንያት በእያንዳንዱ ትምህርት ክፍል መኖር ያለበት የእስፔሻሊስት ሐኪም 25 መሆን ሲገባው በአሁኑ ወቅት በየት/ክፍሉ የሚገኙት ሐኪሞች ከ25 በታች ስለሆነና እንዲሁም የተማሪ ቁጥር ከእጥፍ በላይ የጨመረ በመሆኑና በተደጋጋሚ የቅጥር ማስታወቂያ ቢወጣም ከገበያ ላይ ማግኘት ስላልተቻለ አንድ እስፔሻሊስት ሀኪም በወር 48 ክሬዲት ሰዓት መሸፈን ሲጠበቅበት በዝቅተኛ ስሌት 71.1 ክሬዲት ሰዓት በመሸፈኑ በትርፍነት 23.1 ክሬዲት ሰዓት ወይም 69.3 ሰዓት በወር ስለሚሠራ በየወሩ የትርፍ ሰዓት ክፍያ እንደሚከፈለው እንገልጻለን፡፡ በተጨማሪም በአሁኑ ወቅት ዩኒቨርሲቲዉ ለአንድ እስፔሻሊስት ሀኪም እየተከፈለ ያለው የትርፍ ሰዓት ክፍያ ሌሎች ክልሎችና ዩኒቨርሲቲዎች ከሚከፍሉት ጋር ስነጻጸር የእኛ በጣም አናሳ በመሆኑ ወጣት ሀኪሞችን መሳብ ይቅርና ያሉትንም ማቆየት አለመቻሉን እያሳወቅን ቀደም ሲል በኦዲት የተገኘ ግኝት ሲሆን ያለውን ችግር በተደጋጋሚ በኦዲት ግኝት መልስ ላይ ያሰወቅን መሆኑንና ክፍያው ከቆመ ተማሪዎችን የሚያስተምር ሐኪም ስለማይኖር እስከአሁን ድረስ ክፍያውን ማቆም ያልተቻለ መሆኑን እየገለጽን በተደጋጋሚ የቅጥር ማስታወቂያ ቢወጣም ከገበያ ላይ ማግኘት እንዳልተቻለ ማስታወቂያ የወጣበትን ማስረጃ (የ2008 እና የ2009 ዓም ቅጥር ማስታወቂያ) አምስት ገፅ አያይዘን ያቀረብን መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

1.1.3.1 ግኝት፤በወጪ የተመዘገበ የውሎ አበል ቅድሚያ ክፍያ፤

የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቁጥር ሲ.ሰ.ሚ.30/ጠ13/40/883 በ29/10/04 የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ ያስተላለፈ ሲሆን በተላለፈው መመሪያ መሰረት የውሎ አበል ክፍያ መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- በዩኒቨርሲቲው **ላይዘን ቢሮ** በቅድሚያ የተከፈለው ውሎ አበል ብር 22,226.00 በተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ ሰራተኞች ከመስክ በሚመለሱበት ጊዜ የውሎ አበል ማወራረጃ ቅጽ ተሞልቶና በሚመለከተው ኃላፊ ፀድቆ በወጪ መመዝገብ ሲገባዉ አላግባብ በቀጥታ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ የሂሳቡ ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ቀን	የተከፈለው ሰራተኛ ስም	የወጪ ማ/ቁጥር	የገንዘብ መጠን
1	08/09/09	ሣራ ሰርሞሎ	603593	2,688.00
2	01/09/09	አስቴር አስፋው	603586	1,240.00
3	13/08/09	ሣራ ሰርሞሎ	603582	2,148.00
4	01/07/09	በየነ ፍቅሬ	603563	2,980.00

5	12/06/09	አልማዝ አበበ	0126362	1,490.00
6	29/07/09	ጌታቸው ታምሩ	0126376	895.00
7	21/10/09	ሱንጥለ አብዱልቃድር	603507	1,490.00
8	21/10/09	ጌታቸው ታምሩ	603509	895.00
9	6/10/09	መዘኖር ሰይፉ	603502	1,790.00
10	09/10/09	ሣራ ሰርሞሎ	603505	2,685.00
11	21/09/09	ጌታቸው ታምሩ	0126387	895.00
12	30/09/09	አስቴር አስፋው	603599	1,240.00
13	30/09/09	አልማዝ አበበ	603598	1,790.00
			ድምር	22,226.00

1.1.3.2 ስጋት፤

የውሎ አበል ቅድሚያ ክፍያ የውሎ አበል ማወራረጃ ቅጽ ሳይሞላ በወጪ የሚመዘገብ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክን ያደርጋል፡፡

1.1.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

የውሎ አበል ክፍያ መንግስት ባወጣው መመሪያ መሰረት እንዲፈጸም የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

1.1.3.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

ማንኛውም ሰራተኛ የውሎ አበል መውሰድ የሚኖርበት ከመሄዱ በፊት በተንጠልጣይ ወይም አድቫንስ ፔይመንት ሆኖ ከመንገድ ሲመለስ የሚወራረድ መሆን እንዳለበት ግልጽ ነው፡፡ ሆኖም ግን አልፎ አልፎ አስቸኳይና አጣዳፊ የስራ ሁኔታ ሲፈጠር ሰራተኞች ስራቸውን አጠናቀው ሲመለሱ ክፍያዎች የሚፈፀሙበት ሁኔታ ስለሚፈጠር የተከሰተ ክፍተት ስለሆነ በቀጣይ የማስተካከያ እርምጃ የሚወሰድበት ይሆናል፡፡

1.1.4.1 ግኝት፤ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል፤

በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የቀን ውሎ አበል መመሪያ (ሰኔ 2004 ዓ.ም) ክፍል ሁለት አንቀጽ 5.1 ማንኛዉም የመንግስት ሰራተኛ ከመደበኛ የስራ ቦታዉ ወደ ሆነ ሌላ ስራ ቦታ ለስራ ሄዶ እለቱን መመለስ ካልቻለ በስራ ተሰማርቶ ቁርስ፣ ምሳና እራት በተመደበባቸዉ የክልል ከተሞች ዞኖች እና ወረዳዎች የውሎ አበል ተመን መሰረት መከፈል እንዳለበት ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ፤

- **የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት** ከኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የተላኩ የጤና ኤክስቴሽን ባለሙያዎችን ለ16 ቀን ለማሰልጠን ከክልሉ ጤና ቢሮ ጋር ውል የገባ ሲሆን ከክልሉ ከተገኘው ገቢ ላይ በ02/13/2008 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 620449 ብር 156,250.00 እና በ17/12/2008 በባንክ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 620419 ብር 120,279.00 በድምሩ ብር 276,999.00 ከዋናዉ ግቢና ከቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የተውጣጡ የዩኒቨርሲቲው አመራሮች ወደ ሶኮሩና

ሊሙ ወረዳዎች የሄዱበት በሚል በቀጥታ ወጪ ለእያንዳንዳቸዉ የ32 ቀን ውሎ አበል የተከፈላቸው ሲሆን በውሉ መሰረት ስልጠናዉ የሚካሄደው ጅማ ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ሆኖ እያለ ወደ ወረዳዎች መጓዝ ያስፈለገበትን ሁኔታ የሚገልጽ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ የክፍያውን አግባብነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

1.1.4.2 ስጋት፤

ማንኛውም ክፍያ በመንግስት መመሪያ መሰረት የማይፈጸም ከሆነ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡

1.1.4.3 የማሻሻያ ሃሳብ፤

የተጠቀሰው ክፍያ አግባብነት ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድና የውሎ አበል ክፍያ በመመሪያው መሠረት እንዲፈጸም ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ ይገባል፡፡

1.1.4.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

ለኦሮሚያ ጤና ቢሮ ኤክስቴሽን ሠራተኞች ሥልጠና ከተቋሙ ጋር በተገባው ውል መሰረት በሁለት ዙሮች በተካሄዱ ሥልጠናዎች ወቅት የዩኒቨርስቲው ኃላፊዎች ለሥልጠናው ስኬት ከቅድመ ዝግጅት ጀምሮ እስከ ስልጠናው መጠናቀቅ ከፍተኛ የማስተባበር ሥራ ስለሰሩ የተከፈላቸው መሆኑንና በጀቱም ከመደበኛ በጀት ሳይሆን በፕሮጀክት ውሉ መሰረት ከጤና ቢሮው ከተከፈለ የአገልግሎት ክፍያ እንደሆነ እየገለፅን ከኦዲት አስተያየቱ ተገቢ ትምህርት የተወሰደና ወደፊት ተመሣሣይ ስህተቶች የማይፈፀሙ መሆኑን ጭምር እንገልፃለን፡፡

1.2. የዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ፣

1.2.1.1 ግኝት፤ በኮፒ ማስረጃ የተወራረደ ክፍያ፤

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት ስለመንግስት ገንዘብ ክፍያ አንቀጽ 9 ተራ ቁጥር 7 ላይ ለተገዛ ዕቃ ወይም አገልግሎት ለሂሳብ ማወራረጃ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ኦሪጅናል ደረሰኝ መሆን እንዳለበት ይገልጻል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- **በተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ** በቀን 01/03/09 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 80781 ብር 13,813.57 የትራንስፖርት ክፍያ ለህንድ መምህራን የተከፈለ ሲሆን ለሂሳብ ማወራረጃነት ከወጪ ሰነዱ ጋር የተያያዘው የአውሮፕላን ቲኬት ኮፒ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

1.2.1.2 ስጋት፤

በቅጂ (ኮፒ) ማስረጃ የወጪ ሂሣብ የሚወራረድ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ ለምዝበራ ሊዳረግ ይችላል፡፡

1.2.1.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፤**

ተገቢ ማስረጃ መቅረቡ ሳይረጋገጥ የወጪ ሂሳብ እንዳይወራረድ እና እንዳይመዘገብ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል። ለተጠቀሱትም ሂሳቦች ኦሪጂናል የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞደል 19) እና የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ሊቀርብለት ይገባል።

1.2.1.4 **የሥራ አመራሩ ምላሽ፤**

የተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ ለህንድ መምህር የተከፈለው የአውሮኘላን ትኬት ትክክል ነው፤ ኮፒ ነው በወቅቱ አኛም ጠይቀነው በዚሁ ምክንያት ክፍያው ዘግይቶበት ነበር፤ ነገር ግን መምህሩ አዲስ በመሆኑ እና አሰራሩን ባለመረዳት ለእኔ ይህ ነው የተሰጠኝ በማለቱ ክፍያውን ፈፅመናል። መምህሩም አንድ ወር እንደሰራ በህመም ምክንያት ሥራውን አቋርጦ ወደ ሀገሩ በመመለሱ ደረሰኙን በወቅቱ እንዲስተካከል ማድረግ አልተቻለም። በመሆኑም በተሰጠን አስተያየት ለሚቀጥለው ጥንቃቄ እናደርጋለን።

1.2.2.1 **ግኝት፤ ከክፍያ ላይ ተቀናሽ ያልተደረገ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤**

በገዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 27/2002 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ ወኪሉ ታክስ ከሚከፈልበት ግብይት ላይ የታክሱን ሂሳብ ተቀናናሽ የሚያደርገው የአንድ ጊዜ ግብይት ዋጋ ከብር 5,000.00 (አምስት ሺህ) በላይ ሲሆን ነው። የግብይቱ ዋጋ ብር 5,000.00 እና ከዚያ በታች ከሆነ ወኪሉ የታክሱን ሂሳብ ጭምር ለታክስ ከፋዩ መክፈል እንዳለበት ይገልጻል። የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- **በጤና ኢንስቲትዩት** በቀን 25/11/08 በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 134400 ለተማሪዎች መማሪያ ክፍል የፕሮጀክተር ማስቀመጫ ግዥ ለሄኖክና ዮሀንስ ብረታ ብረት ኢንጂነሪንግ ኃላ/የተ/የህ/ሽ/ማህበር ብር 97,500.00 ክፍያ ሲፈጽም የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 14,625.08 (97,500*0.15) ተቀናሽ በማድረግ ለገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ፈሰስ ማድረግ ሲገባ ከነታክሱ ለድርጅቱ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል።
- **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት** በቀን 30/05/2009 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 251149 ብር 27,026.37 እና በቀን 29/03/2009 በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 555936 ብር 35,999.90 በድምሩ ብር 63,026.27 ለDSTV ካርድ ግዥ ለመልቲ ቸይዝ አፍሪካ ክፍያ ሲፈጸም የቅደመ-ግብር ክፍያ (Withholding tax) ብር 1,071.44 (53,572.23*2%) እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 9,453.94 (63,026.77*15%) በድምሩ ብር 10,525.38 ከድርጅቱ ተቀናሽ ተደርጎ ለመንግስት ገቢ መደረግ ሲገባዉ አላግባብ ከነታክሱ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል።

1.2.2.2 **ስጋት፤**

ክፍያዎችን በመንግስት መመሪያ መሰረት አለመፈጸም የህግ ጥሰት ከመሆኑም በተጨማሪ መንግስት ሊያገኝ የሚችለውን ገቢ ሊያሳጣ ይችላል፡፡

1.2.2.3 **የማሻሻያ ሀሳብ፤**

ያልተሰበሰበው የመንግሥት ግብር ተሰብስቦ ለሚመለከተው መ/ቤት ገቢ እንዲደረግና ለወደፊቱም የመንግስት ደንብና መመሪያ ተጠብቆ ሥራዎችን ማከናወን ይገባል፡፡

1.2.2.4 **የሥራ አመራሩ ምላሽ፤**

በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የተፈፀመው ክፍያ የተማሪዎች የDSTV አገልግሎት ክፍያን የተመለከተ ሲሆን በወቅቱ የክፍያው ጥያቄ ዘግይቶ በመቅረቡና ጉዳዩም የተማሪዎች አንገብጋቢ ጥያቄ ስለሆነ ክፍያውን ማዘግየት አስቸጋሪ በመሆኑ ጅማ በሚገኘው ወኪል አማካኝነት ክፍያው ሊፈፀም ችሏል፡፡ ሆኖም የድርጅቱ አሰራር የተጠቀሱትን የግብር ዓይነቶች በብሔራዊ ባንክ በኩል የሚያስተናግድ በመሆኑ ያንን በወቅቱ ለመፈፀም ተማሪዎች የDSTV አገልግሎቱን በጣም የሚፈልጉበት ወቅት ስለነበር ችግር እንዳይከሰት የተፈፀመ መሆኑን እየገለፅን ኢንስቲትዩቱ ለድርጅቱ ደብዳቤ እንደሚፅፍ አረጋግጧል፡፡

1.2.3.1 **ግኝት፤ ከክፍያ ላይ ተቀናሽ ያልተደረገ የቅደመ-ግብር ክፍያ (Withholding tax)፤**

የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀፅ 24 ግብር ቀንሶ ገቢ የማድረግ ስርዓት ስር በቁጥር 1 በአንድ ጊዜ ግዥ ወይም በአንድ የዕቃ አቅርቦት ውል ከብር 10,000 (አስር ሺህ) በላይ ለሆነ የዕቃ አቅርቦት ከሚፈፀም ክፍያ ላይ የቅደመ-ግብር ክፍያ (Withholding Tax) 2% ቀንሰዉ ማስቀረት እንዳለባቸዉ ይገልፃል፡፡ መ/ቤቶች የሰበሰቡትን ግብር በየወሩ መጨረሻ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ፈሰስ ማድረግ እንዳለባቸዉ ይገልፃል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- **በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት** ለተለያዩ አቅራቢ ድርጅቶች የግዢ ክፍያ ሲፈጸም የቅደመ-ግብር ክፍያ (Withholding Tax) 2% በድምሩ ብር 16,834.38 ከድርጅቶቹ ተቀናሽ ተደርጎ ለመንግስት ገቢ መደረግ ሲገባዉ አላግባብ ከነታክሱ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

ተ/ቁ	ቀን	ቫዉቸር ቁጥር	የተከፈለው ድርጅት ስም	የተገዛው እቃ	የክፍያው መጠን	የታክስ መጠን
1	23/08/09	251452	Reliable enducational plc	የመጽሀፍ	152,435.00	3,048.70
2	13/10/09	468344	ወይራ ሜዲካል ሰፕላየር plc	መድሃኒቶች	110,940.00	2,218.80
3	13/10/09	468345	ብሉቲጅ ፋርማቲካል ኃ.የ.ማ	መድሃኒቶች	199,736.00	3,994.72
4	15/10/09	251489	ማባን ትሬንግ ኃ.የ.ማ	መድሃኒቶች	183,779.00	3,675.58
5	15/10/09	251490	ብሉቲጅ ፋርማቲካል ኃ.የማ	መድሃኒቶች	194,829.00	3,896.58
				ድምር	841,719.00	16,834.38

1.2.3.2 ስጋት፤

ክፍያዎች ሲፈጸሙ የመንግስት ግብር ተቀናሽ አለማድረግ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡ በተጨማሪም የመንግስት ግብር በወቅቱ እንዳይሰበሰብ ሊያደርግ ይችላል፡፡

1.2.3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

የግዢ ክፍያ ሲፈጸም ቅድመ-ግብር ክፍያ ተቀናሽ ተደርጎ ለሚመለከተው የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ገቢ እንዲደረግ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

1.2.3.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

ከመጽሐፍና ከመድሐኒት የWithholding tax አይሰበሰብም የሚል የተሳሳተ ግንዛቤ በግዥ ክፍሉና በሂሳብ ሰራተኞች አካባቢ ስለነበር ችግሩ ሊከሰት የቻለ መሆኑን ባደረገው ማጣራት ማረጋገጡን ኢንስቲትዩቱ ገልፆ ለድርጅቱ ደብዳቤ እንደሚፅፍ አረጋግጣÿል፡፡

1.2.4.1 ግኝት፤ በዋጋ ማቅረቢያ የተፈጸመ ግዢ፤

በፌዴራል መንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/2001 አንቀጽ 33/2 እና ሰኔ 2002 በወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ መመሪያ አንቀጽ 15/2 መሠረት በአዋጁና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግሥት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልጽ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው፣ በአዋጁ አንቀጽ 33/4 መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች በግዥ አዋጁ ወይም በግዥ መመሪያው የተዘረጉ የግዥ ሥርዓቶችን ለመሸሽ በአንድነት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን የዕቃ፣ የግንባታ ወይም የአገልግሎት ግዥዎችን መከፋፈል እንደሌለባቸው እንዲሁም፣ በመመሪያው አንቀጽ 24/1 እና 24/4 መሠረት ሊታቀዱ ያልቻሉና ወዲያውኑ ጥቅም ላይ የሚውሉ ወይም በጅምላ ሊገዙ ያልቻሉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዋጋቸው በመመሪያው በተጠቀሰው መሠረት በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ዘዴ ለመፈፀም እንደሚቻል የተገለጸ ቢሆንም የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- ግዥዉ በዕቅድ ተይዞ በግልፅ ጨረታ በጥቅል መገዛት ሲገባው በዋጋ ማቅረቢያ የግዥ ዘዴ **በዋናው ግቢ** ብር 2,902,161.39፤ **በሶሻል ሳይንስ ኮሌጅ** ብር 542,362.15 እና **በጤና ኢንስቲትዩት** ብር 1,312,070.76 በድምሩ በብር 4,756,594.30 የተለያዩ ዕቃዎች ግዢ ተፈጽሟል፡፡ ዝርዝሩ **በአባሪ ቁጥር** 1 ተመልክቷል፡፡

1.2.4.2 ስጋት፤

ግዥ በአዋጁና መመሪያው መሠረት ካልተፈፀመ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ቁጠባ፣ የአፈፃፀም ብቃትና ውጤታማነትን ማስገኘቱን ማረጋገጥ አይቻልም፣ የመንግሥት ገንዘብ ለምዝበራ ሊጋለጥም ይችላል፡፡

1.2.4.3 የማሻሻያ ሃሳብ

ግዢዎች በግዢ መመሪያ መሠረት እንዲፈጸሙ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ተገቢ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል።

1.2.4.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

እነዚህ ግዥዎች በአመቱ ውስጥ በተለያየ ግዜ የተፈፀሙ የተለያዩ አይነት እቃዎች ግዥዎች የዓመቱ ጥቅል ድምር እንጅ የግዢ ጥያቄዎቹ በአንድ ጊዜ ቀርበው ሆን ተብሎ ተከፋፍሎ የተከናወኑ ግዥዎች አይደሉም። ከእነኝህ ግዥዎች ውስጥ ለምሳሌ በግልፅ ጨረታ የተካተቱ ከተማሪዎች ምግብ ቤት፤ ከተማሪዎች መታወቂያ ካርድ መቀየር በማስፈለጉ እንዲሁም ለአዲስ ገቢ ተማሪዎች ተጨማሪ መታወቂያ ካርድ እንዲሰራላቸዉ እንዲያስችል እና መጠኑም አነስተኛ በመሆኑ እንዲሁም አንዳንድ ለጥገና የሚፈለጉ የግንባታ እቃዎች የጨረታ ሂደቱ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ጊዜ የማይሰጥ በመሆኑ አስቸኳይነቱ በዩኒቨርስቲዉ ፕሬዚደንትና በሚመለከታቸዉ ታምኖበት የተፈፀመ ግዢ ነዉ።

1.3. ለቋሚ ዕቃዎችና መሠረተ-ልማት ሥራዎች ክፍያ፤

1.3.1.1 ግኝት፤ ያልተመዘገበ የግንባታ መያዣ ተከፋይ ሂሳብ፤

የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 5 ፊደል ሀ እና ሠ መሰረት ማንኛውም ወደፊት ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸው የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብነት መያዝ እንዳለበትና የተከፋይ ሂሳብ እንቅስቃሴዎች በእለቱ በሂሳብ መዝገብ ላይ መመዝገብና በሂሳብ ሌጀር ላይ መወራረስ እንዳለባቸው ይገልፃል። የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- በድምሩ ብር 22,898,293.64 የግንባታ መያዣ ሂሰብ (Retention) ከህንጻ ስራ ተቋራጮች የተቀነሰ ቢሆንም በመመሪያው መሰረት በሂሳብ መደብ 5061 በተከፋይ ሂሳብ ተመዝግቦ ሪፖርት መደረግ ሲገባዉ ምንም አይነት የሂሣብ ምዝገባ ያልተከናወነና የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ውስጥ ተካቶ ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል። የሂሳቡ ዝርዝር **በአባሪ ቁጥር** 2 ተመልክቷል።

1.3.1.2 ስጋት፤

- ከክፍያ ላይ ተቀናሽ የተደረገ ተከፋይ ሂሳብ ባለመመዝገቡ የዩኒቨርሲቲው የወጪ እና የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገፅታውን እንዳያሳይ ያደርጋል።
- ኮንትራክተሮች ያስያዙትን የመያዣ ሂሣብ ለማወቅ አያስችልም።

1.3.1.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

ያልተመዘገበው የመያዣ ሂሣብ ተመዘግቦ በሂሣብ ሪፖርት እንዲካተት የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም ለሥራ ተቋራጮች ክፍያ ሲፈጸም የሚቀነሱ የመያዣ እና የቅድሚያ ክፍያ ተመላሽ ሂሣቦች በአግባቡ እንዲመዘገቡ ተገቢ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ ይገባል፡፡

1.3.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

ከግንባታ ኘሮጀክቶች ክፍያ ጋር ተያይዞ የግንባታ □መ□□ ሂሳብ (Retention) በተከፋይ ሂሳብነት ተመዝግቦ በሂሳብ ሌጀር ላይ መዝግበን በሂሳብ ሪፖርታችን ላይ አካተን ስናቀርብ የቆየን ቢሆንም ከሪፖርቱ ወስጥ እንዲወጣ እና በሌጀር ላይ ለረጅም አመታት ተንጠልጥሎ መታየት የሌለበት መሆኑን የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በገለፀልን መሠረት የወጣ ቢሆንም የውስጥ የመከታተያ ስርዓት በመዘርጋት የምንሰራ ሲሆን በቀጣይ በምን መልኩ መስራት እንዳለብን ጥያቄውን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ማኒስቴር አቅርበን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ምዝገባውን እንድናከናውን በጽሁፍ በሰጠን ትዕዛዝ መሰረት ምዝገባው ከቆመበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን □እያንዳንዱን የግንባታ □ሮ□ክት የመያዣ ሂሳብ በመመዝገብ ሂሳቡን ያስተካከልን መሆኑን እየገለፅን ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተላከውን የትዕዛዝ ደብዳቤ አንድ ገፅ በአባሪነት አያይዘናል፡፡

2. የተሰብሳቢ ሂሳብ

2.1 ግኝት፤

በፌዴራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ 5/2003 አንቀጽ 8/4 መሰረት የተሰብብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳቦች ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት የዩኒቨርሲቲው የተሰብሳቢ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ከተመለከተው ሂሳብ ውስጥ በጊዜ ገደቡ ያልተወራረደና ከ1 ወር እስከ 14 ዓመት በተሰብሳቢነት የቆየ ብር 1,411,723.83 የሚገኝ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዝርዝሩም፤

- በሂሳብ መደብ 4201 ከተለያዩ ተቋማትና ግለሰቦች የሚፈለግ ከ1 ወር እስከ 14 ዓመት የቆየ ብር 453,470.36 የሚገኝ መሆኑ፤
- በሂሳብ መደብ 4203 ሌሎች ቅድመ ክፍያ ብር 861,924.60 የሚገኝ መሆኑ፤
- በሂሳብ መደብ 4211 ብር 96,328.87 ከግዥ ሰራተኞች የሚፈለግ ቅድሚያ ክፍያ የሚገኝ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

2.2 ስጋት፤

በቅድሚያ ክፍያ ወጪ የተደረገው ሂሳብ በጊዜ ገደቡ ውስጥ አለመወራረዱ ለሌላ ስራ ሊውል የሚችለው የመንግስት ገንዘብ በግለሰቦች፤ በመ/ቤቶችና ድርጅቶች ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ ሂሳቡ ወደ ማይወራረድበት ደረጃ ሊደርስ ይችላል፡፡

2.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

ተሰብሳቢ ሂሣቦች በወቅቱ እንዲወራረዱ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራሩ አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

2.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

- □ብር 241,760.50 በፍርድ ቤት ውሳኔ ታግዶ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ□እግዱ ተነስቶ ለዩኒቨርሲቲው ስለተወሰነ የታቀ□□ ሂሳብ ሲለቀቅ በተሰብሳቢ የተያዘው ሂሳብ የሚስተካከል መሆኑን□እንገልጻለን፡፡
- ብር 58,870.04 ለ14 □መታት የቆየ ቢሆንም ጉዳዩ ለረጅም አመታት በፍርድ ቤት ሲታጁ ቆይቶ ለዩኒቨርሲቲው ቢወሰንም የአከፋፈል አፈፃፀም ላይ በንብረትነት ጥያቄ የቀረበበት መኖሪያ ቤት ህጋዊነት ተቀባይነት ባለማግኘቱ በሰበር ችሎት ውድቅ ሆኗል፡፡
- በሂሳብ መ□ብ 4203 ላጁ □ሚታ□□ ሂሳብ ብር 89,445.44 እንዲሁም በሂሳብ መደብ 4201 ላጁ □ሚታ□□ ብር 7,571.80 በ□ቅላላ□ ብር 97,017.24 ለህግ አገልግሎታችን ተመርቶ ክስ ለመመስረት በሂደት ላይ የሚገኝ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

3. የበጀት ሂሳብ፣

3.1. ግኝት፣

የዩኒቨርሲቲው የበጀት አስተዳደር እና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 12 መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ለዩኒቨርሲቲው በ2009 በጀት ዓመት የተፈቀደለት በጀትና በሥራ ላይ የዋለው ሂሣብ ሲነጻጸር በተለያዩ ሂሣብ መደቦች ከመደበኛ በጀት ብር 10,367,290.33 እና ከውስጥ ገቢ 742,742.28 በድምሩ ብር 11,110,032.61 ሥራ ላይ ያልዋለ (ያልተሰራበት) በጀት ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ **በአባሪ ቁጥር 3 ቀርቧል፡፡**

3.2 ስጋት፤

የተፈቀደው በጀት በዕቅዱ መሠረት ሥራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ የዩኒቨርሲቲውን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ በሌሎች መ/ቤቶች ሊሰራበት የሚችለውን በጀት በዩኒቨርሲቲው ስም ተይዞ እንዲቆይ ያደርጋል፡፡

3.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

ዩኒቨርሲቲው የተፈቀደለትን በጀት በመንግስት የፋይናንስ አዋጅ መሰረት በስራ ላይ እንዲያውል የተቋሙ ሥራ አመራር በበጀት አጠቃቀም ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

3.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

የጅማ ዩኒቨርሲቲ የ2009 በጀት ዓመት በጀት አጠቃቀም በተመለከተ ስራ ላጁ □ልኘ፟ለ ተብሎ ስለተፀለና□ □ተሰ□ ፅበረ መልስ፡-

- በእርቴታ ለገቡ ዕቃዎች የተከፈለው 2 በመቶ ብቻ በመሆኑ ገንዘብ አጠቃቀም ዝቅተኛ መሆኑ፤
- በበጀት እጥረት ምክንያት ተጠይቆ የመጣው ገንዘብ ለ□አ□ ስለማጁበቃ ለ2010 በመተላለኙ፤
- አቅራቢ ድርጅቶች በገቡት የጊዜ ውል መሠረት ንብረትና አገልግሎታቸውን በወቅቱ ማቅረብ ባለመቻላቸው፤
- በማክቀአ ፅዴ ንብረት ለማቅረብ የተመረጡት ድርጅቶች በወቅቱ ባለመቅረባቸውና ግዥው ለቀጣይ በጀት ዓመት በመተላለኙ፤ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

4. የንብረት አያያዝና አመዘጋገብን በተመለከተ፤

4.1 ግኝት፤

የዩኒቨርሲቲዉ የንብረት አያያዝ፤ አጠባበቅ እና አመዘጋገብ በአዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 በተገለፁት ሁኔታዎች እና ድንጋጌዎች መሠረት መከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

4.1.1 በዋናው ግቢ፤

- መወገድ ሚገባቸው 3 የዉሃ ማፍያ ማሽኖች፣ የተለያዩ ቁርጥራጭ ብረቶች፣ 116 ኢፕሰን ፕሪንተሮች፣ 216 ዲቫይደሮች፣ 118 ታጣፊ ወንበር እና 11መኪናዎች ያልተወገዱ መሆኑ፤
- በተማሪዎች ምግብ ቤት ከ10 አመት በላይ አገልግሎት ሳይሰጡ የተቀመጡ 4 (አራት) ፍሪጆች የሚገኙ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

4.1.2 በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፤

- የተለያዩ UPS በቁጥር 433፣ የኮምፒዩተር ጠረጴዛዎች በቁጥር 78 እና ወንበሮች በቁጥር 50 ያለአገልግሎት የሚገኙ መሆኑ፤
- የዉሃ ማጠራቀሚያ ፕላስቲኮች በቁጥር 323 ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤፤

- የተለያዩ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፣ ኮምፒዩተሮች፣ የእንግዳ ወንበሮች እና UPS ሳይወገዱ በአሮጌ ዕቃዎች ግምጃ ቤት (ሳልቫጅ ስቶር) የሚገኙ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

4.1.3 በስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፤

- ቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች በአንድ ላይ ተቀላቅለዉ በአንድ መጋዘን ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣
- ከሶስት አመት በላይ ያለአገልግሎት የተቀመጡ በርከት ያሉ የሴቶች ጫማና አልባሳት በዕቃ ግምጃ ቤት የሚገኙ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

4.1.4 በግብርናና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ፤

- ቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች በአንድ ላይ ተቀላቅለዉ በአንድ መጋዘን ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣
- በብልሽት አገልግሎት የማይሰጥ አንድ የማባዣ ማሽን በዕቃ ግምጃ ቤት የሚገኝ መሆኑ፣
- በተማሪዎች ምግብ ቤት አገልግሎት የማይሰጡ የተበላሹ አራት ስቶቮች የሚገኙ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

4.2 ስጋት፤

ንብረቶች በመመሪያው መሠረት ካልተጠበቁና በወቅቱ ሥራ ላይ ካልዋሉ አላግባብ ሊጠፉና ሊበላሹ ይችላል፡፡

4.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር በንብረት አያያዝና አጠባበቅ ላይ የታዩ የአሰራር ግድፈቶች እንዲስተካከሉ አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

4.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

የዋናው ግቢ፤

- መወገድ ያለባቸዉ 3 የዉሃ ማሽኖችን በተመለከተ ዩኒቨርስቲዉ ከሌሎች እቃዎች ጋር ለማስወገድ ጨረታ አዉጥቶ ለእነዚህ እቃዎች ገዢ ያልተገኘ በመሆኑ ሲሆን እሁን ግን ድጋሚ ለማስወገድ በሂደት ላይ ስንሆን ዳግም ካልተሸጠ ግን ለዩኒቨርስቲዉ ሰራተኞች ክበብ መጠነኛ አገልገሎት እንዲሰጥ ለማድረግ እየተሞከረ ነዉ፡፡
- የተለዩ የተቆራረጡ ብረታ ብረቶችን በተመለከተ ዩኒቨርስቲዉ በራሱ ማስወገድ ስለማይችል ዝርዝራቸዉን ለመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት አሳዉቆ በወጣዉ ጨረታ መሠረት አሸናፊዉ ድርጅት ለዩኒቨርስቲያችን ቢገለፅልንም አሸናፊዉ ድርጅት መጥቶ ከማየት በስተቀር ሊያነሳልን ባለመቻሉ የተፈጠረ ሲሆን ይህንንም ለሚመለከተዉ የመንግስት አካል አቅርበናል፡፡
- 11 መኪናዎችን በተመለከተ በተመሳሳይ መልኩ በጨረታ የማስወገዱ ሂደት በመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በኩል ተደጋጋሚ ጨረታ ወጥቶ ለመሸጥ እየተሞከረ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ግን 4ቱ የተሸጡ ስለመሆኑ ርክክብ እንድናደረግ ከመንግስት ግዢና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ደብዳቤ ደርሶናል፡፡

- በተማሪዎች አገልግሎት የሚገኙ ፍሪጆች እቃዎቹን በቀጥታ ከማስወገድ ይልቅ ባለሙያ ተፈልጎ ተጠግነዉ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ታስቦ በመሆኑ ይህም በቅርቡ ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን ተጠግነዉ አገልግሎት መስጠት ካልቻሉ ግን ለማስወገድ እንሰራለን፣፣

<u>የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፤</u>

- ከዩፒኤስ በስተቀር ሌሎቹ የተዘረዘሩት አንዛኞቹ ንብረቶች በአገልግሎት ላይ መዋላቸውን እና በቅርቡ ስራ የሚጀምሩት ላቦራቶሪዎች ደግሞ ዩፒኤሱን በአገልግሎት ላይ የሚያውሉት ይሆናል፡፡
- ያገለገሉ ንብረቶችን በተመለከተ በኢንስቲትዩቱ ከዚህ በፊት የእቃ ግምጃ ቤት በአግባቡ ባለመደራጀቱ በ2010 ዓ.ም በአዲስ መልክ የማደራጀት ስራ እየተሰራ በመሆኑ በግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በተላለፈው ሰርኩላር መሰረት በእቃ ግምጃ ቤት የሚገኙትን ንብረቶች በመለየት ለማስወገድ በዝግጅት ላይ ነን፡፡

<u>የግብርናና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ፤</u>

- የኮሌጁ ቋሚ ንብረትና አላቂ እቃዎች በአንድ ላይ ተቀላቅለው በአንድ መጋዘን ውስጥ መገኘታቸው ካለው የመጋዘን እጥረት የተነሳ የቋሚና የአላቂ ንብረትን በግራና ቀኝ በመለየት እየተጠቀምን የምንገኝ ሲሆን በየጊዜው የሚገቡትን ቋሚ እቃዎች ወዲያውኑ ለክፍሎች የምናሰራጭ ሲሆን ለወደፊት ግን ግምጃ ቤቱን ለሁለት በማካፈል የቋሚና የአላቂ ንብረት መጋዘን የመለየት ስራ ጀምረናል፡፡
- የማባዣ ማሽኑን በሚመለከት ከክፍሎች ተበላሽቶ የተመለሰ ሲሆን ጥገናውን ከሚያከናውኑ ባለሙያዎች የተሰጠን አስተያየት የማሽኑ አንዳንድ እቃዎች በገበያ ላይ ባለመገኘታቸው ምክንያት የቆየ ቢሆንም ለወደፊቱ የሚወገድበትን ሁኔታ የሚመቻች ይሆናል፡፡
- አራቱን ስቶቮችን በሚመለከት በብልሽት ምክንያት አገልግሎት እየሰጡ ባለመሆኑና በአካባቢው ባሉ ባለሙያዎች መጠገን ባለመቻሉ የተቀመጡ ሲሆን የተሻለ ባለሙያ በማፈላለግ ተጠግኖ ስራ ላይ እንዲውል የሚደረግ ይሆናል፡፡

<u>የስፔሻላዝድ ሆስፒታል፤</u>

- በመጋዘን የሚገኘው የሴቶች ጫማና አልባሳት ጥናቱ ተጠናቆ የሚወገድበት መንገድ ተመቻችቷል፡፡

5. <u>ተሽከርካሪዎች፤</u>

5.1 <u>ግኝት፤ የኪ/ሜ ቆጣሪያቸው (ጌጅ) የማይሰራ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ፤</u>

የፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ 32/2004ዓ.ም ክፍል 3 አንቀጽ 9/1 እና 2 መ/ቤቶች የተሽከርካሪዎችን የነዳጅ ፍጆታ ለመከታተል እና መዝግቦ ለመያዝ እንዲረዳቸው የተሽከርካሪዎች የኪ/ሜ ቆጣሪ (ጌጅ) የተሟላና በትክክል የሚሰራ መሆኑን በየጊዜው በመከታተል ማረጋገጥ እንዳለባቸውና እያንዳንዱ ተሽከርካሪ የፈጀውን የነዳጅ መጠን ከሸፈነው የኪ/ሜ መጠን ጋር እየተገናዘበ ተገቢው ሪፖርት በየወሩ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚሁ መሰረት ኦዲት ሲደረግ፤

- የዩኒቨርሲቲው 7 (ሰባት) ተሽከርካሪዎች የኪ/ሜ ቆጣሪ (ጌጅ) የማይሰራ መሆኑና ተሽከርካሪዎቹ በሄዱበት ኪ/ሜ ተገምቶ ነዳጅ የሚሞላ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ የተሽከርካሪዎቹ ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	የሰሌዳ ቁጥር	የተሽከርካሪው አይነት	የሊብሬ ቁጥር
1	ኢት 4-09229	ማርቸዲስ አውቶቢስ	E020754
2	ኢት 4-16027	ዶዎ አውቶቢስ	0033631
3	ኢት 4-11302	ሚስት ቡሽ ሮዝ	E020731
4	ኢት 4-02645	አይቬኮ አውቶቢስ	E005986
5	ኢት 4-02471	ቶዮታ ደብል ገቢና	E006186
6	ኢት 4-02474	አይሱዙ ደብል ገቢና	E006272
7	ኢት 4-13994	ዶዎ የውሃ ቦቴ	E0093241

5.2 ስጋት፤

የኪ/ሜ ቆጣሪ ጌጃቸው የማይሰራ ተሽከርካሪዎችን ለሥራ ማሰማራት የነዳጅ ፍጆታን ለመቆጣጠር ስለማያስችል የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

5.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

የኪ/ሜ ጌጃቸው የተበላሹ ተሽከርካሪዎች ጌጅ እንዲጠገኑ ወይም በአዲስ እንዲቀየሩ በማድረግ የተሽከርካሪዎች የነዳጅ ፍጆታ ተሽከርካሪው በሊትር በአማካይ በሚጓዘው ርቀት መጠን መሆኑ በየጊዜው ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይገባል፡፡

5.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

ዩኒቨርሲቲው የሚጠቀምባቸው ተሽከርካሪዎች ጌጅ የሌላቸውን ቴፀ እንዲኖራቸው ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ሲሆን ነገር ግን ዕቃው ገበ□ ላጁ ባለመቶኘቱ ምክንያት ያለውን አገልግሎት ክፍተት ለመሸፈን ተሽከርካሪዎች ስራ ላይ እንዲውሉ ያደረግን ሲሆን የነዳጅ አጠቃቀማቸውን በተመለከተ በአንድ አይነት ዘርፍ አገልግሎት የሚሰጡ የኪሎ ሜትር ቆጣሪ ካላቸው ተሽከርካሪዎች የነዳጅ አ□ታ ጋር በማነፃፀር ቁዓዓር እየተከናወነ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

6. ልዩ ልዩ፤

6.1 ግኝት፤የውስጥ ኦዲት ክፍል የሰው ኃይልን በተመለከተ፤

የፌዴራል መንግሥት የውስጥ ኦዲት መመሪያ ቁጥር 7/2003 አንቀጽ 8/2 የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍል ተገቢው የሙያ ብቃት፤ ዕውቀትና ክህሎት ባላቸው ባለሙያዎች የማደራጀትና በቂ የትምህርት ዝግጅትና አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ ያካበተ የውስጥ ኦዲት ኃላፊ የመመደብ የመ/ቤት የበላይ ሃላፊ ሃላፊነት እንደሆነ ይገልፃል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ፤

- በዩኒቨርሲቲው የሰው ኃይል መዋቅር መሠረት 12 የኦዲት ባለሙያዎች የሚያስፈልግ ሲሆን በአሁኑ ወቅት 3 የኦዲት ባለሙያዎች ሲኖሩ ከዩኒቨርሲቲው የውስጥ ኦዲት የሰው ኃይል መዋቅር ጋር ሲነፃፀር 9 የኦዲት ባለሙያዎች በቅጥር ያልተሟሉ መሆኑ ታውቋል፡፡

6.2 ስጋት፤

የውስጥ ኦዲት ክፍሉ ተገቢው የሙያ ብቃት፣ ዕውቀትና ክህሎት ባላቸው ባለሙያዎች ካልተደራጀ በዩኒቨርሲቲው የተዘረጋውን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ጠንካራና ደካማ ጎኑን በመለየት ለዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር በተገቢው መንገድ ሳይቀርብ ይችላል፡፡

6.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

የውስጥ ኦዲት የሥራ ክፍል የሚጠበቅበትን አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ የሰው ኃይሉ ተገቢው የሙያ ብቃት፣ ዕውቀትና ክህሎት ባላቸው ባለሙያዎች እንዲሟላ ተገቢው ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

6.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

የዩኒቨርሲቲው የውስጥ ኦዲት መጠናከር በዩኒቨርሲቲው የተሻለ የቁጥጥር ስርዓት እንዲዘረጋ በማድረግ ረቶት ከፍተኛ □ቀሜታ ያለው መሆኑን ዩኒቨርሲቲው ይገነዘባል፡፡ ባለፋት ዓመታት የኦዲት አገልግሎቱን ለማጠናከር የስራ ክፍሉን ብቃት ባለው ባለሙያ ለማደራጀት ተደጋጋሚ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ ይሁን እንጂ የስራ መደቦቹ ከሚጠይቁት የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ ጋር በተያያዘ □ሚ□□ □ቅዓር ማስታወቂያዎች መሠረት በቂ ሰራተኛ ማፅኘት ባለመቻላችን በተለያዩ ዓመታት የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸውን ምሩቃን ቀጥረን ለማሰራት ተደጋጋሚ ሙከራዎችን በማድረግ የተወሰኑ ምሩቃንን ቀጥረን አገልግሎቱን ለማጠናከር ከፍተኛ ጥረት ቢደረግም እነኚህ ምሩቃንም ቢሆኑ ከሚከፈላቸው የደመወዝ ስኬል አነስተኛ መሆኑን የተለያዩ የጥቅማጥቅም ፖለኬጆች አለመኖር ጋር ተያይዞ አብዛኛዎቹ የተወሰኑ ወራትን ብቻ አገልግለው ስራቸውን እ□ለቀቁ ሄ□ዀል፡፡
በመሆኑም በገበያ ላይ የስራ መደቦቹ የሚጠይቁትን የትምህርት ዝግጅትና አግባብ ያለው የስራ ልምድ ሊ□ሟሉ □ሚችሉ ባለሙያዎችን ማግኘት ባለመቻላችን ምክንያት ችግሩ የቀጠለ መሆኑን ግንዛቤ እንዲወሰድ እየጠየቅን ዩኒቨርሲቲው በአሁኑ ሰዓትም ቢሆን ዳይሬክቶሬቱን በሰው ሃይል ለማደራጀትና ለማጠናከር ጥረት እ□ደረገ ሲሆን በሃገር ዓቀፍ ደረጃ እየተከናወነ ያለው አዲሱ የስራ መደቦች የስራ ደረጃ ምዘናና ደመወዝ አወሳሰን ስርዓት ተግባራዊ ሲደረግ የተሟላ መፍትሄ ይገኛል ብለን እናምናለን፡፡

7. ከ2003 እስከ 2008 በጀት ዓመት የሕጋዊነት ኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ ያልተወሰደባቸው ግኝቶች በተመለከተ፤

7.1 ግኝት፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ክፍል አምስት አንቀጽ 17/3 መሠረት ኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ

የመውሰድ ግዴታ አለባቸው። የወሰዱትን እርምጃ እና አርምጃ ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለጽ ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ እንዳለባቸው ይደነግጋል። ሆኖም ግን ዩኒቨርሲቲው ከ2003 እስከ 2008 በጀት ዓመት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሠረት ከዚህ በታች በተገለጹ ግኝቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ ታውቋል።

በ2003 በጀት ዓመት ኦዲት የተገኙ ግኝቶች፤

- የተማሪዎች መዝናኛ ክበብ በመንገድ ግንባታ ሥራ ምክንያት በመፍረሱ ለካሳ ክፍያ ተብሎ ብር 4,517,544.47 ከተቋሙ ሂሳብ ወጪ በማድረግ በመዝናኛ ክበቡ ስም በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገ ገንዘብ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

በ2004 በጀት ዓመት ኦዲት የተገኙ ግኝቶች፤

- ለኮሚዩኒቲ ት/ቤት አላግባብ የተከፈለው የካሳ ክፍያ ብር 8,812,578.98 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

በ2008 በጀት ዓመት የተገኙ ግኝቶች፤

- መምህራን ወደ ተለያዩ ቦታዎች ለሲፐርቪዥን የሄዱበት የውሎ አበል ክፍያ ሲፈጸም በአጠቃላይ በዩኒቨርስቲው ብር 234,214.00 የውሎ አበል በብልጫ የተከፈለ መሆኑ፤
- የምርምር ስራ የሚያስፈልገውን የሁለተኛ ዙር በጀት ብር 120,362.00 በአቶ ኤልያስ ቃዲ ስም ወጪ ከተደረገው ገንዘብ በምርምር ስራው ለተሳተፉ መምህራንና የጤና ባለሙያዎች የውሎ አበል ሲከፈል በአንድ ቀን ሁለት ጊዜ ለሠራተኞቹ በመከፈሉ ብር 36,724.00 አላግባብ የተከፈለ መሆኑ፤
- የግንባታ ሥራ ያቋረጡ ሥራ ተቋራጮች የጉዳት ካሳና የማቴሪያል ዋጋ በጠቅላላው ብር 63,077,064.58 ለዩኒቨርሲቲው ያልከፈሉ መሆኑ፤
- በድምሩ USD 247,098.78 ዋጋ ያላቸው ዕቃዎች ገቢ ያልተደረጉ እና የንብረት ተረካቢ ኮሚቴ ንብረቶቹ እንደጎደሉና እንዳልመጡ የገለፀበት ሁኔታ ቢኖርም ንብረቶቹ ያልመጡበት ምክንያት ተጣርቶ ለዩኒቨርሲቲው እንዲላኩ ክትትል መደረጉን የሚገልጽ ማስረጃ ለኦዲቱ ሥራ አለመቅረቡ፤
- ዩኒቨርሲቲው ሰበታ ከተማ ለሚያሰራው የእንግዶች ማረፊያና የሎጅስቲክ ማዕከል የሚያገለግል የግንባታ ግብዓቶች (የተለያዩ ብረቶች) ከቢንያም ሃይለግዚ አጠቃላይ አስመጪ ግዥ ፈጽሞ በጠቅላላው ብር 4,439,379.50 የተከፈለ ሲሆን ለግንባታው ሥራ የተገዙት ብረቶች፣ ጠጠርና አሸዋ ከአመት በላይ ያለምንም አገልግሎት ለብልሽት በተጋረገ መልኩ የተቀመጡ መሆኑ፤

የንብረት አያያዝና አጠባበቅን በተመለከተ፤

የዋናው ግቢ

- ለህንፃዎች መለያ ቁጥር ያልተሰጠ እና ተመዝግበዉ ያልተያዙ መሆኑ፣
- የሚወገዱ የተለያዩ ዕቃዎች (ጎማዎች፣ የተለያዩ ቁርጥራጭ ብረቶች፣ 1032 ቪጂኤ ኬብል፣ 46 የተለያዩ አይነት ኮምፒዩተር፣ 961 የተለያዩ አይነት ሞኒተሮች፣ 11 መኪኖች እና 324 መጠቀሚያ ጊዜያቸዉ ያለፈባቸዉ የተለያዩ ኬሚካሎች) ያልተወገዱ መሆኑ፤

የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት

- በአላቂ ዕቃ ግምጃ ቤት ዉስጥ የተለያዩ ሞደል ያላቸዉ የፕሪንቴር ቀለሞች 38A ብዛት 46፣ 96A ብዛት 56፣ 98A ብዛት 1፣ 61X ብዛት 8 ከሁለት ዓመት በፊት ተገዝተው የገቡ ሲሆን እስካሁን ጥቅም ላይ ሳይዉሉ የሚገኙ መሆኑ፣
- የግዥ ክፍሉና የንብረት ክፍሉ የሚናበቡበት ቅጽ የማይጠቀሙ መሆኑ፣
- በግብርና ኮሌጅ ሁለት የዉሃ ፓምፕ ማሽን ከአስር ዓመት በላይ በግብርና ኮሌጅ በመቀመጡ ለብልሽት እየተዳረገ የሚገኝ መሆኑ፤
- በተመላሽ ዕቃ ግምጃ ቤት በርካታ ዕቃዎች (ፍሪጅ፣ ኮምፒውተሮች፣ ዩፒኤስ፣ ፍራሾች፣ ሎከሮች፣ ፕሪንተሮች እና የመሳሰሉ) አገልግሎት መስጠት የሚችሉትና የተበላሹት በባለሙያ ሳይለዩ ለረጅም ጊዜ በንብረት ክፍል የተቀመጡ መሆኑ፣
- ያገለገሉ ንብረቶች ተመላሽ ሲደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ የሚቆረጥላቸው ቢሆንም አዲስ ገቢ ከሚደረግ ንብረት ለመለየት እንዲያስችል ያገለገሉ ንብረቶች ገቢና ወጪ ማህተም የተዘጋጀ ቢሆንም በአግባቡ ስራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፣

7.2 ስጋት፤

በተሰጠ የኦዲት አስተያየት መሠረት የማስተካከያ እርምጃ አለመውሰድ በኦዲት ወቅት የታዩ የአሰራር ግድፈቶች እንዳይታረሙ ከማድረጉም ባሻገር ተጠያቂነትን ያስከትላል።

7.3 የማሻሻያ ሀሳብ፤

በኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሚ እናሳስባለን።

7.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ፤

በ2003 በጀት ዓመት ኦዲት የተገኙ ግኝቶች፤

- ቀደም ሲል ዩኒቨርሲቲው ካሳውን የከፈለበት መነሻና ለገ/ኢ/ት/ ሚ/ር ፈሰስ ያልተደረገበት ምክንያት ተብራርቶ መመሪያ ከገ/ኢ/ት/ሚ/ር ተጠይቆ ነበር የሚሰጠውን ውሳኔ ተግባራዊ እንደምናደርግ በመርሃ ግብሩ ዝግጅት ወቅት ገልፀናል፡፡

በ2004 በጀት ዓመት ኦዲት የተገኙ ግኝቶች፤

- ለኮሚዩኒቲ ት/ቤት የተከፈለው የካሳ ክፍያ ከተማሪዎች መዝናኛ ጉዳይ ጋር ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ደብዳቤ ተፅፎ መመሪያ እየተጠየቀበት ያለ ጉዳይ ነው፡፡

በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት የተገኙ ግኝቶች፤

- የውሉ አበል ቅጽ ሲሞላ የሰዓት አሞላሉ ላይ የተፈጠረ ስህተት በመሆኑ ለወደፊት አሞላሉ በጥንቃቄ እንዲሆን መመሪያ ተሰጥቷል፡፡
- በጤና ሳይንስ ኮሌጅ ተመራማሪው የውሎ አበል ቅጹን ሲሞሉ የተፈጠረ ክፍተትና በወቅቱም በኮሌጁ የፋይናንስ ባለሙያ እጥረት በመኖሩ ሲሆን ለወደፊት እርምት እንዲደረግ ሆኗል፡፡ ነገር ግን በሁለቱም ኮሌጆች ክፍያው ለማጭበርበር የተደረገ አለመሆኑን የኮሌጆቹ ሃላፊዎች ማረጋገጫ ሰጥተዋል፡፡
- ከተለያዩ ኮንስትራክሽንኖች በጠቅላላው ብር 63,077,064.58 የግንባታ ሥራ ያቋረጡ ሥራ ተቋራጮች ለዩኒቨርሲቲው የጉዳት ካሳ ያልከፈሉትን በሚመለከት የቴዎድሮስ አበራ ከዚህ ግኝት በፊት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ ተመስርቶ ክርክር ላይ መሆናችንን በማኔጅመንት ሌተር ምላሽ ላይ ማስረጃውን ያያያዝን ቢሆንም በድጋሚ አንድ ገፅ አባሪ ገፅ 55 ላይ እዚህ አያይዘናል፡፡ ለኦሮሚያ ውሃ ስራዎች ለቅድመ ክፍያ ዋስ ለሆነው ለኦሮሚያ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የመጀመሪያ ደብዳቤ ተፅፎ ተቋራጩ ከዩኒቨርሲቲው የሚጠይቀው ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ስላለ ጉዳዩ በውይይት እንዲፈታ ጥያቄ አቅርቧል፡፡ (ድርጅቱ የፃፈው ሶስት ገፅ ደብዳቤአባሪ ማስረጃ ገፅ 56-58 ይመልከቱ)፡፡
- በእርዳታ የመጡ እቃዎች ጉድለትን በተመለከተ ለእርዳታ ሰጪ ድርጅቱ ደብዳቤ የተፃፈለት ቢሆንም ምላሽ አልተገኘም፡፡ ተጨማሪ ክትትል እንዲደረግ ከበላይ አመራር ለስፔሻላይዝድ ሆስፒታሉ በደብዳቤ መመሪያ ተሰጥቷል፡፡
- በሰበታ ከተማ ለሚሰራው የእንግዶች ማረፊያና የሎጅስቲክ ማዕከል የተገዙ የግንባታ ግብዓቶችን በሚመለከት ግንባታው የዘገየበት መሰረታዊ ምክንያት የግንባታ ፈቃድ ከከተማው ምክር ቤት ማግኘት አለመቻሉ መሆኑን በማኔጅመንት ሌተር ምላሽ ዶኩመንት ላይ ማብራራታችን ይታወቃል፡፡ ቀደም ሲል ግንባታው እንዲጀመር ተወስኖ ግንባታውን የሚከታተል አማካሪ ቅጥር ጨረታ ላይ መሆናችንን በመርሃግብሩ ዝግጅት ዶኩመንት ላይ

ገልፀናል፡፡ ከአማካሪ ድርጅት በተጨማሪ የተቋራጭ ድርጅት ጨረታ ወጥቶ አሸናፊውን ለመለየት የሁለቱም ጨረታዎች ዶክመንት እየተገመገመ ነው፡፡

<u>የንብረት አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ የተሰጠ ምላሽ</u>፤

<u>ዋናው ግቢ</u>፤

- ለህንፃዎች መለያ ቁጥር መስጠት በ2010 በጀት ዓመት ለመተግበር በእቅድ ይዘን እየተንቀሳቀስን ነው፡፡

<u>ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት</u>፤

- የፐሪንተር ቀለሞችን በተመለከተ ቀለሙን የሚጠቀሙ ማሽኖች በመበላሸታቸው ሲሆን ጥቅም ላይ ለማዋል ለመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ድጋፍ ለማድረግ ታቅዷል፡፡
- የነፍስ ወከፍ ካርድ ቀደም ሲል በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የተከፈተ ሲሆን ከ2010 ጀምሮ የንብረት አስተዳደርን ኮምፒዩተራይዝድ የማድረግ ስራ ስለሚጠናቀቅ በኢንስቲትዩቱ ደረጃ ለግለሰቦች ካርድ የሚከፈት ይሆናል፡፡
- እስካሁን በቅጽ ባይሆንም ሁለቱ ክፍሎች በቃልና በደብዳቤ ልውውጥ ይሰሩ የነበረ ሲሆን በቅርቡ ቅጽ ተዘጋጅቶ ስራ ላይ የሚውል ይሆናል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት ለተደረገልን መልካም የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

አባሪ ቁጥር 1. **በዋጋ ማቅረቢያ የተፈጸመ ግዢ፤**

በዋናው ግቢ፤

ተ.ቁ	ቀን	የቫውቸር ቁጥር	የተገዛው እቃ	አቅራቢው ድርጅት	የገንዘብ መጠን
1	09/10/09	424438	የኤልክትሪክ ገመድ	ፈቲያ አስራር የህንጻ መሳሪያ	199,237.50
2	05/10/09	848860	የኤልክትሪክ ገመድ	እርጎ ባህሩ የህንጻ መ/ መደበር	198,720.00
3	28/09/09	843775	የኤልክትሪክ ገመድ	እርጎ ባህሩ የህንጻ መ/ መደበር	184,000.00
4	02/10/09	424437	የኤልክትሪክ ገመድ	ቁልቢ ገብርኤል	170,683.38
5	27/10/09	446010	የመኪና ጎማ	ዘላለም መኮንን አስመጪ	88,550.00
6	26/10/09	424180	የመኪና ጎማ	ታርኳ መኮንን የመኪና መ/መደብር	194,810.00
7	04/09/09	843863	የቢሮ ፋርኒቸር	ፍቅሩ ፈርኒቸር /ዘላለም እሸቱ	168,190.96
8	15/09/09	424077	የቢሮ ፋርኒቸር	ፍቅሩ ፈርኒቸር /ዘላለም እሸቱ	112,380.16
9	04/09/09	848702	የቢሮ ፋርኒቸር	ፍቅሩ ፈርኒቸር /ዘላለም እሸቱ	199,003.89
10	12/12/08	850235	የጥገና እቃዎች	የተለያዩ ድርጅቶች	199,950.50
11	19/01/09	614083	የጥገና እቃዎች	የተለያዩ ድርጅቶች	199,323.75
12	30/03/09	423090	የጥገና እቃዎች	የተለያዩ ድርጅቶች	198,950.00
13	26/06/09	424063	የጥገና እቃዎች	የተለያዩ ድርጅቶች	199,737.75
14	12/05/09	424451	የፕላስትክ ወንበር	የተለያዩ ድርጅቶች	199,520.00
15	04/07/09	424414	የአይሲቲ እቃዎች	የተለያዩ ድርጅቶች	196,178.50
16	28/03/09	422748	የጽዳት እቃዎች	የተለያዩ ድርጅቶች	192,925.00
				ድምር	2,902,161.39

በሶሻል ሳይንስ ኮሌጅ፤

ተ.ቁ	ቀን	የደረሰኝ ቁጥር	የተገዛው ዕቃ	አቅራቢው ድርጅት	የገንዘብ መጠን
1	28/07/09	96996	ካሜራ ከነአክሰሰሪው	ወርልድ ተኳንዶ	199,845.85
2	22/03/09	96997	የሙዚቃ መሳሪያዎች	ሄኖክ ካሳዬ	199,750.00
3	14/04/09	543384	የተለያዩ አልባሳት	አስራት ታደሰ	90,836.30
4	29/05/09	601234	የሰዓት መቆጣጠሪያ	አይሰንስ ቴክኖሎጂስ	51,930.00
				ድምር	542,362.15

በጤና ኢንስቲትዩት፤

ተ.ቁ	ቀን	የደረሰኝ ቁጥር	የተገዛው ዕቃ	አቅራቢው ድርጅት	የገንዘብ መጠን
1	24/04/09	897060	የኮምፒዉተር ጠረጴዛዎች	ፍቅር ፈርኒቸር	96,000.00
2	12/07/09	897073	ህትመት ግዢ	ርሆቦት አታሚዎች	80,500.00
3	25/11/08	134400	የፕሮጀክተር ማስቀመጫ	ሄኖክና ዮሃንስ የብረታ ብረት	97,500.00
4	30/04/09	897061	የቢሮ እቀዎች የተገዛበት	ጎይቶም ገ/ዮሃንስ የቢሮ እቃዎች	199,990.00
5	13/10/09	897458	ለኬሚካል ግዥ የተፈፀመ	ብሉቲጂ ፋርማሲዩቲካልስ	188,874.59

6	02/09/09	897078	የጥርስ መገልገያ እቃዎች	አኬዴንት የህክምና መሳርያዎች	198,874.50
7	02/09/09	897082	የፀሀይና የሙቀት መከላከያ	ቢኒያም ጥለት አስመጭ	153,499.92
8	14/10/09	899026	የፀሀይና የሙቀት መከላከያ	ዘላለም ኩማ የቢሮ ማስዋብያ	195,252.75
9	27/10/09	899062	የላብራቶሪ ኬሚካሎች	አፍሪ ሜድ አጠቃላይ አስመጪ	101,579.00
				ድምር	1,312,070.76

አባሪ ቁጥር 2. ያልተመዘገበ የግንባታ መያዣ ተከፋይ ሂሣብ፤

ተ.ቁ	ቀን	የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	በወጪ የተመዘገበ የገንዘብ መጠን	የመያዣ ሂሳብ (retation) የገንዘብ መጠን
1	30/06/09	601499	14,687,983.63	667,635.62
2	27/07/09	843903	19,226,812.83	873,946.04
3	29/06/09	849581	30,311,447.42	1,377,793.06
4	03/01/09	850723	6,818,639.87	309,938.04
5	21/02/09	601465	10,782,347.76	490,106.72
6	26/03/09	849619	5,419,109.40	246,323.15
7	29/03/09	849823	26,933,144.44	1,224,233.84
8	21/02/09	849752	4,877,294.56	221,695.21
9	29/06/09	849582	24,034,529.01	1,092,478.59
10	14/07/09	849197	10,722,638.32	487,392.65
11	6/10/09	853041	5,714,241.41	259,738.25
12	17/12/08	838799	5,475,684.03	248,894.73
13	18/05/09	842721	22,146,253.77	1,006,647.90
14	03/06/09	842686	15,948,338.71	724,924.49
15	04/13/08	838877	7,530,440.67	239,645.00
16	04/04/09	849622	6,995,030.33	317,955.92
17	08/02/09	849452	5,090,113.31	191,087.24
18	21/02/09	849363	10,542,650.53	479,211.39
19	14/07/09	849740	71,102,119.10	3,231,914.50
20	30/06/09	839992	12,443,778.39	565,626.29
21	6/12/09	850675	7,111,490.84	323,249.58
22	03/12/08	838694	5,145,653.97	233,893.36
23	08/05/09	849777	4,848,574.73	220,389.76
24	27/04/09	842718	10,353,761.90	470,625.54
25	28/04/09	849672	13,023,889.75	591,994.99
26	03/01/09	839550	18,442,331.02	838,287.77
27	03/01/09	850542	21,241,250.77	965,511.40
28	04/04/09	842017	13,228,138.90	601,279.04
29	29/03/09	849523	17,114,091.61	777,913.26
30	01/03/09	849371	13,985,698.59	635,713.58
31	21/02/09	601464	12,608,713.61	573,123.35
32	14/02/09	849057	18,974,261.02	862,466.41
33	14/07/09	849196	12,394776.77	563,398.94
34	12/07/09	842740	21,631,676.74	983,258.03
		ድምር	**506,906,907.71**	**22,898,293.64**

አባሪ ቁጥር 3. የ2009 በጀት ዓመት የበጀት ማመዛዘኛ፤

የሂሳብ መደብ	የተፈቀደ በጀት (1)	ስራ ላይ የዋለ (2)	ልዩነት 3=(2-1)	ልዩነት በ% 4=(3/1*100)
ያልተሰራበት በጀት (መደበኛ)				
6219	886,953.00	615,956.20	(270,996.80)	31%
6232	5,713,699.00	4,205,558.96	(1,508,140.0)	26%
6233	9,587,670.00	7,771,404.59	(1,816,265.41)	19%
6243	1,879,445.00	1,228,295.54	(651,149.46)	35%
6253	1,343,685.00	1,130,536.09	(213,148.91)	16%
6255	1,357,475.00	1,101,633.98	(255,841.02)	19%
6256	1,325,087.00	1,110,341.67	(214,745.33)	16%
6257	4,859,181.00	4,222,177.60	(637,003.40)	13%
6314	4,800,000.00	0.00	(4,800,000.00)	100%
ድምር	31,753,195.00	21,385,904.63	(10,367,290.33)	33%
ያልተሰራበት በጀት (ካፒታል)				
6124	100,000.00	56,450.00	(43,550.00)	44%
6321	471,839.00	171,838.75	(300,000.25)	64%
6323	552,151,401.30	490,263,525.75	(61,887,875.55)	11%
6326	8,923,000.00	6,122,327.44	(2,800,672.56)	31%
6417	292,150.00	58,708.06	(233,441.94)	80%
6124	100,000.00	56,450.00	(43,550.00)	44%
ድምር	562,038,390.30	496,729,300.00	(65,309,090.30)	12%
ከበጀት በላይ (መደበኛ)				
6313	26,729,014.00	36,515,472.40	9,786,458.40	37%
ድምር	26,729,014.00	36,515,472.40	9,786,458.40	37%
ከበጀት በላይ (ካፒታል)				
6324	222,965,105.70	254,563,841.45	31,598,735.75	14%
ድምር	222,965,105.70	254,563,841.45	31,598,735.75	14%
ያልተሰራበት በጀት (የውስጥ ገቢ)				
6213	1,417,500.00	1,195,744.16	(221,755.84)	16%
6232	500,000.00	204,151.00	(295,849.00)	59%
6313	1,875,000.00	1,649,862.56	(225,137.44)	12%
ድምር	3,792,500.00	3,049,757.72	(742,742.28)	20%